ፍላጎቶች ሊያሟላ የሚችል አይደለም። የሰፊው ሕዝብ ዋነኛ ጥያቄ የፋሽስቱ መንግሥት አገዛዝ እንዲያከትም ማድረግ በመሆኑ፣ በሥልጣን ተንደላቀው የሚጨፍሩት አረመኔዎች በፈቃደኝነት የስቅለት ገመዳቸውን በአንገታቸው የሚያጠልቁ አይሆኑም። ስለዚህም የብዙሃኑ አርሶአደር ጥያቄ መፍትሔ እንዲያገኝ፣ አርሶአደሩ ከብዝበዛና ከጭቆና የሚላቀቅበት ሁኔታ እንዲፈጠር፣ የሥልጣንና የመብት፣ የጉልበቱና የምርቱ ባለቤት እንዲሆን፣ ሰላም እንዲያገኝ፣ ከቤተሰቡና ከሀገሩ እንዳይነጠል፣ በአጠቃላይም የኢትዮጵያ ጭቁን ሠርቶአደሮች ጥቅምና መብት እንዲጠበቅ ሃቀኛ ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ መንግሥት መመሥረት አለበት። የዚህም ዓይነት መንግሥት መሠረቱ ሊጣል የሚችለው በፋሽስቱ መንግሥት የመቃብር ድንጋይ ላይ በመሆኑ ለመብትና ለነፃነት አሁንም ሕዝባዊ ትግልን በንብረት ከማፋፋም ሌላ አማራጭ የለም።

ሃቀኛ ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ
በተራዘመው ሕዝባዊ ትግል ትመሠረታለች!

እናቸንፋለን!!

የ ጎሠፊያ